እማ ደጓ እናቴ ( ሄኖክ የሺጥላ )

እማ ራበሽ ፣ ልጆችሽም
ከማጀትሽ አልቆረሽም
ከእንስራሽ አልጠለቅሽም
እማ መኖር አላየሽም !

እታታዬ ውዷ እናቴ
የሚሞቀው ያ ትከሻሽ
የተላጠው እኔን ሲያዝል
የገረጣው ጠይም ወዝሽ
የጠቆረው ውቡ ገጽሽ
በመከራ በቸነፈር
ተስፋሽ ከመሬት ሲቀበር

እንቅልፍ እምቢ አለኝ እማ
ስለ አንጀትሽ መታጠፍ ፣ ስለ ረሃብሽ ስሰማ !

እናናዬ ደጓ እናቴ
የፍቅር የናፍቆት ጠረን
የተስፋ ፣ የጸሎት ቤቴ

ማ'ጻንሽ ምነው መከነ
እምቢታሽ ምነው ሰከነ
በራብ በቸነፈር ጦስ
ቤትሽን ወረሰው የሎስ
መክሊትሽ ለዛ ጠረንሽ
የዋይ ዋይ ዜና ሆነልሽ!

እአታታዬ ምነው ኩታሽ ፣ ጥበብሽ ድሩ ጠቆረ
ምነው የመቀነትሽ ጥለቱ ተቆጣጠረ
ምነው ቁጭቱ እንደ ሰማይ
ጥቁር አደፍ አረገዘ
ምነው ፊትሽ ትካዜ ፣ በክንዱ ደግፎ ያዘ
ምነው ልጅሽ አንገቱን ከሆድሽ ስር የደፋው
ምን ጥቁር አፈር ስር ፣ አይኑን ተክሎ የጠፋው ?

እታታዬ ደጓ እናቴ
ከጎጆሽ ወጥተሽ በድንኳን
ልጆችሽን ይዘሽ እንኳን
እያየነው ራብሽን
በሰናፍጭ ፣ በቅንጣት ፣ እያዘገምሽ በራሽን
ባጥንትሽ ፣ በባዶ ሆድሽ ፣ ደረቅ ጡት እያጠባሽም
እነ የሎስ ይነጉሩናል ፣ ይሰብካሉ ጥጋብሽን
ዜና አውታሩ እያወራም ፣ ያስብሉሻል አልተራብሽም !

እናናዬ ደጓ እናቴ
እኔን ብለሽ ያሳደግሽኝ
እኔን ሳልል ሳልደርስልሽ
ሳልሰዋ ሳልሞትልሽ
እታታዬ እንቺ እናቴን
መቃብር ከተቱሽ አሉ
ጠግባላች ፤ ተመችቷታል ፤ አልተራበችም እያሉ !

እታታዬ አንቺ እናቴ
ምነው ጥልትሽን ባረገኝ
አፈር ስትልሺ ልሼ ፤
እሾሁን ፤ ራብ ችግሩን ካንቺ ጋ እኩል ቀምሼ
ምነው በሞትኩ እማማዬ
ያይኔ ጥላ ፤ ከለላዬ !

እኔ ብሎ ያሳደገኝ
ምነው አንጀትሽን ባረገኝ !
በራብ አለንጋ ሲገረፍ
አብሬ እኔ እንድገረፍ
ምነው ሆድሽን በሆንኩኝ
ካንቺ በፊት ባንቺ አንጀት ፤ እኔ ላንቺ በተራብኩኝ
እታታዬ ደጓ እናቴ !